# ፕ/ር ጌታቸው በጋሻው ሆድ ብሷቸው ሆድ አስባሱኝ

(ግዜነው ደም መላሽ)

ከሶስት አመት በፊት ይመስለኛል የዩኒቲ ዩንቨረሲቲ የቀድሞው ባለቤት የነበሩት ዶ/ር ፍሰሃ እሸቱ ኢሳትና VOA ላይ ቀርበው በውጭ አዲስ የሽግግር መንግስት መመስረት እንዳሰቡና ስርአቱን በቶሎ (በስድስት ወር ውስጥ) አስወግደው ወደ ሙያዊ ስራቸው መመለስ እንደሚፈልጉ መግለፃቸውን አስታውሳለሁ።መንግስትን መጣል ኮመዲያኖቻችን እንደሚሉት እንደ "ሙዝ መላጥ" አቅልለውብን ስለነበረ እኝህ ባለሀብትና ሙሁር የአሜሪካ ወይም የአንድ ሀያል ሀገር ድጋፍ ቢኖራቸው ይሆናል እንጂ ብለን ጠርጥረን ነበር። ይህንን ቃለ መጠይቅ ካደረጉ ከአንድ ወር ተኩል በኋላ ደግሞ የአቶ መለስ ዜናዊ  ዜና እረፍት ሲሰማ ያሉትን ወደማመኑ ደርሰን ነበር። ቢያንስ ባሰቡት ፍጥነት ሳይሳካላቸው ቀረና ዶ/ር ፍሰሃ እሸቱም "የኢትዮጵያ ብሔራዊ የሽግግር ምክር ቤት" የሚባል ድርጅት መስርተው ወደተራዘመ ትግል ውስጥ ገቡ። የሆነው ሆኖ "በቃ በስድስት ወር ውስጥ ህውሃትን ልንገላገለው ነው" ብለው ተስፋ ሰንቀው ለነበረነው ወገኖች ተስፋችን የውሀ ሽታ ከሆነ ሶስት አመት አልፎ አራተኛውን ይዘናል። ለማንኛውም  ዶ/ር ፍሰሃ  በወቅቱ ከሰጡት ቃለ መጠይቅ እንደተረዳሁት ቅንና ለሀገራቸው ጥሩ ራዕይ ያላቸው ሰው ናቸው።ተሰማርተውበት በነበረው የስራ ዘርፍም ፈር ቀዳጅና ውጤታማ ነበሩ። እንደ እኔ ቅን ሰው ፖለቲከኛ መሆን የሚችልና ከገባበትም የሚቀናው አይመስለኝም። በተለይ እንደነ ስብሀት ነጋ ያሉ ሸፍጥና ተንኮልን የሕይዎታቸውም የትግላቸውም መመሪያ ባደረጉ ሰዎች የተፈጠረን ስብስብ  ለመታገል ቅንነትና ሚዛናዊነት ብዙም አዋጭ አይደሉም።ቅንነትና ምክንያትዐዊ አቀራረብ ህውሃት ሰዎች ዘንድ እንደ ጅልነት ነውና የሚወሰደው።ለማንኛውም ትግል ለማድረግ የሚነሳ ቡድን ስለሚታገለው አካል በቂ የሆነ የስነልቦና፣ የሰው ሀይልና የማቴሪያል ዝግጅት ማድረግ ይገባዋል።ጠላት ለሚለው አካልም ተመጣጣኝ የሆነ   ክብደት ሊሰጥና ያንን ሊመክትና ሊያሸንፍ የሚያስችል በቂ ዝግጅት ማድረግ አለበት ብየ ነው የማምነው። ይህ ማለት ጠላትን አግዝፎ በማሳየት ታጋዮችን ተስፋ ለማስቆረጥ ሳይሆን ጠላትን አሳንሶ ገምቶ ሽንፈት ላይ ላለመውደቅ ይረዳልና ነው።

ሰሞኑን ደግሞ ኢሳትና ቪዥን ኢትዮጵያ የተባለ ድርጅት የተወሰኑ የፖለቲካ ፖርቲ መሪዎችንና ምሁራኖችን አሰባስበው ስለ ነገዋ ኢትዮጵያ ለመምከር "ሽግግር ዲሞክራሲና አንድነት" በሚል እርዕስ  የሁለት ቀን ኮንፈረንስ መደረጉ ይታዎቃል። ዝግጅቱን በንግግር  የከፈቱትና የቪዥን ኢትዮጵያ መስራችና ፕሬዚዳንት የሆኑት ፕሮፌሰር ጌታቸው በጋሻው በንግግራቸው መሀል እንባ እየተናነቃቸው ንግግራቸውን  ሲያቋረጡና ሲያለቅሱ  ስመለከት በጣም ነው ያዘንከት።ሆድ ብሷቸው እኛንም ሆን እንዲብሰን አደረጉን። ኢትዮጵያ ለካ አልፎ አልፎም ቢሆን  እንዲህ ለሀገራቸው ቅን ልቦናና ብሩህ አህምሮ ያላቸው ምሁራን አሏት? እንድንልና ተስፋም እንድንሰንቅ ነው ያደረጉን። ህውሃት በተከለብን የዘርና የቋንቋ ፖለቲካ "እኛ"ና "እነሱ" በሚል ተቦድኖ ሀገሩን ለዘራፊ፣ እወክለዋለሁ የሚለውን ማህበረሰብ ለአሳሪ፣ለገራፊና ለገዳይ ትቶ በየጥጋጥጉ እንካ ሰላንትያ እየተጫወተ ያለውን ወገን ለማሰባሰብና ተቀራርቦ እንዲመክር፣ የጋራ አጀንዳ  ቀርፆ የጋራ ጠላቱ ላይ እንዲዘምት ለማስቻል እንባውን እያፈሰሰ የሚማፀን ምሁር ማየት በርግጥም ደስ የሚል ነገር ነውና የሁሉም ድጋፍ የሚያሻው  ጉዳይ ነው።

እንደተረዳሁት ከሆነ ጉባዔው ቀጣይነት አለው።በርግጥም ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ውስብስብ ችግር በአንድና በሁለት ስብሰባዎች የሚፈታ ጉዳይ አይደለም። ተደጋጋሚና እልህ አስጨራሽ የሆኑና የሁሉንም ማሕበረሰብ ስሜቶች የሚያንፀባርቁ ውይይቶች ማድረግ የግድ ይላን። ዛሬ ላነሳው የፈለኩት ሀሳብ ታዲያ በኔ እይታ ኮንፈረንሱ ነበሩበት የምላቸውን መጠነኛ ክፍተቶች ለመጠቆምና ቢቻል በቀጣይ በሚደረጉ ተመሳሳይ ምክክሮች ላይ መካተት አለባቸው የምላቸውን አንድ ሶስት ነጥቦች ለማንሳት ነው።

የመጀመሪያው ክፍተት የሚመስለኝ የጉባዔው አዘጋጆች ለፖናሊስትነት(የመወያያ ወረቀቶችን አቅራቢዎች) ከመረጧቸው ሙሁራን መካከል የታሪክ ሰዎችን (historian) ቢያካትት መልካም የነበረ

ይመስለኛል። ከቀረቡት ምሁሮች አጭር ገለፃ እንደተረዳሁቱ የኢኮኖሚክስ፣የፍልስፍና፣ የአካውንቲንግና የፖለካል ሳይንስ ምሁራኖች ናቸው የተጋበዙትና የመወያያ ንግግሮችን ያደረጉት። ዛሬ ኢትዮጵያዊያን ካሉብን መጠነ ሰፌ ችግሮች አንዱና በእኔ እምነት ዋነኛው በቀደመው የሀገራችን ታሪክ ላይ የጋራ መተማመን ማጣታችን ይመስለኛል። ባለፉት 40ና 50 ዓመታት የታሪክ ሰዎቻችን እንዲገለሉና የኢትዮጵያን ታሪክ ፖለቲከኞቻችን እንደ ፖለቲካ አጀንዳዎቻቸው ለአላማቸው በሚያመቻቸው መልኩ ብቻ እንደፈለጋቸው ሲተርኩት መክረማቸው ይታዎቃል። ይህ ደግሞ የዛሬውን ትልድ በተቃርኖ እንዲቆምና ሁሉም በፖለቲካ መሪዎቹ የተተረከለትን ብቻ እንዲያምንና በኢትዮጵያን መካከል የጋራ መግባባት እንዳይፈጠር ከፍተኛ መሰናከል መሆኑ ይታዎቃል።ይህንን መሰሉ ክስተትም በኮንፈረሱ ላይ ሲስተዋልም ታዝበናል።

ሀሳቡን ለማጠናከር አንዷት ምሳሌ ለማንሳት ከፖለቲካ መሪዎች መካከል የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ግምባር የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ የሆኑትና ድርጅቱን ወክለው የቀረቡት አቶ ሌንጮ ባቲ አሳብ ልጥቀስ።አቶ ሌንጮ ባቲ የኢትዮጵያዊያን የችግራችን ምንጭ ነው በማለት እንደዋና መከራከሪያ ሀሳብ ይዘውት ከቀረቡት ነጥብ አንዱ “ኢትዮጵያ ከሌሎች አፍሪካ ሀገሮች በተለየ መልኩ የተሰራችው ከሰሜን በመጡ ኢትዮጵያዊያን በመሆኑ የሰሜኑ ባህል በሌሎች ላይ ተጭኖል” የሚል ሀሳብ ነው። ኢትዮጵያ የተሰራችው በኢትዮጵያዊያን ነው።ይሄ ምንም ስህተት የለበትም።እንደ ሕዝብ ልንራኮበትም የሚገባ ትልቅ የመንፈስ ሀብታችን ነው። በአለም ገናና ከነበሩት ወደ አምስት ከሚጠጉ ኢምፖየሮች የአንደኛው የአክሱም ኢምፖየር ባለቤት እንደመሆናችን ሀገራችንን እራሳችን ለመስራት አቅምም ችሎታውም ያለን ሕዝቦች ነበርና። በኢትዮጵያ የረዥም ታሪክና በዚህም በነበረው የኢትዮጵያዊያን እንቅስቃሴ የባህል መወራረስ አይኖርም አይባልምና የባህልም ተፅኖ ሊኖር ይችላል። እኔ ያልገባኝና ምናልባት የታሪክ ምሁራን ቢኖሩ ኖሮ ማብራሪያ ይሰጡበት ነበር የምለው አቶ ሌንጮ ደጋግመው “ኢትዮጵያ የተሰራችው ከሰሜን በመጡ ፣ ከሰሜን በመጡ” እያሉ ያቀረቡበት ትንታኔ ነው። እንደገባኝ እየጠቀሱ ያለው ከአፄ ምኒሊክ በኋላ ስለምናውቃት “ዘመናዊዋ ኢትዮጵያ” ይመስለኛል። ይህ እንግዲህ በዘመናዊዋ ኢትዮጵያ ምስረታ ወቅት የኦሮሞው ማህበረሰብ ተሳታፊ አልነበረም የሚለውን የኦነግ ትርክት ለመድገም ይመስለኛል።የዚህ አይነት የታሪክ ትንታኔ ደግሞ እን ፕሮፌሰር ጌታቸው በጋሻው በሕዝቦች መካከል ሊፈጥሩ ላሰቡት መቀራረብ እንቅፋት የሚሆንና የተለመደው የታሪክ ማወራረድ ውስጥ የሚከት ነው።

ለማንኛውም እኔ ባለኝ መጠነኛ የታሪክ ግንዛቤ ይችን “ዘመናዊዋ ኢትዮጵያ” የሰሩት አፄ ምኒሊክ የሸዋ ንጉስ የነበሩና አያት ቅድማያቶቻቸውም ከዛው ከሸዋ መሆናቸውን ነው። ጳውሎስ እኞኞ እንደዘገበው “ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ከአባታችው ከሸዋው ንጉሥ ኃይለ መለኮት ሣህለ ሥላሴና ከእናታቸው ወይዘሮ እጅጋየሁ ለማ አድያም ነሐሴ ፲፪ ቀን ፲፰፻፴፮ ዓ.ም ደብረ ብርሃን አካባቢ አንጎለላ ከሚባል ሥፍራ ተወልደው፤ በአንጎለላ መቅደላ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ክርስትና ተነሡ “ነው የሚለው።እንግዲህ ሸዋ የኢትዮጵያ ሰሜን ነው ካልተባል አፄ ሚኒሊክ ከሸዋ እየተነሱ ነበር ወደ ሰሜንም ሆነ ወደ ሌላው ኢትዮጵያ ግዛት ያሉትን ንጉሶች ያስገበሩት። በማስገበሩ ሂደትም ወታደሮቻቸው ውስጥም ሆነ በአላፊነት ደረጃም ቢሆን የኦሮሞ ተወላጆች ነበሩባቻው። ወደ ቆየው ዘመን ከሄድን ደግሞ በ12ኛው ክፍለ ዘመን አጼ ይኩኖ አምላክ የዘመኑን የዛግዌ ስርወ መንግሥት በመቃወም ሲነሱ ከክርስቲያን አማራዎች አገር ከሸዋ እንደተነሱ እና ቀድሞውንም የአክሱም ነገሥታት በጉዲት መነሳት ሥልጣናቸውን ሲለቁ ከዛች ንግሥት በመሸሽ ተከታዮቻቸውንና ቤተ ሰባቸውን ደብቀው የኖሩት በዚሁ በሸዋ ውስጥ እንደ ነበር ነው ታሪክ የዘገበው።እንደ ክብረ ነገሥት (አንቀጽ 39) አተራረክ ከወሰድነው ደግሞ ሸዋ ከክርስቶስ ልደት በፊትም ጀምሮ የአጼ ቀዳማዊ ምኒልክ ክፍላገር የነበረ እንደሆነ ነው የሚጠቀሰ።ስለዚህ ኢትዮጵያን የሰሩት ኢትዮጵያዊያን አነሳሳቸው ከመሀል ኢትዮጵያ ከሸዋ ነው። የወቅቱን የፖለቲካ ትርክት አሳማኝ ለማድረግ ሲባል ብቻ የሌለና ያልነበረ ነገር እያወሩ ለመጪው ትውልድ ማስተላለፉ አላፊነት የጎደለው ፣የታሪክ ሰዎች እርምት ሊሰጡበት የሚገባ ጉዳይ ይመስለኛል። ይህን መሰል የፖለቲካ ትንታኔ የሚያራርቅ እንጂ የሚያቀራርብ አይደለምና።

ሁለተኛው ክፍተት ሆኖ ታየኝ በፖናሊስትነትም ሆነ በተሳታፊነት ወጣቶችን በብዛት ያለማየታችን ጉዳይ ነው።ባብዛኛው ተሳታፊ 60ዎችን የተሻገረ ይመስለኛል።ወጣት ስል ላለፉት ወደ 30 ለሚጠጉ ዓመታት የልዩነትና የጥላቻ ፖለቲካ የተሰራበትን ወጣት ለማለት ነው። እነ ኤርሚያስ ለገሰ አይጨምርም። ከፖለቲካው ሰሪዎች ውስጥ ስለሆኑ/ስለነበሩ ።ይህንን ሀሳብ የማነሳው እነዚህ በእድሜ የበሰሉትና ለሀገራቸው ቅን አመለካከት እንዳላቸው የምንረዳላቸው መህራኖች የዎቅቱ የወጣቶች የፖለቲካ አሰላለፍ በርግጥ በአግባቡ ተረድተውታል ወይ? የሚል ጥያቄ ስላጫረብኝ ነው።በሽታን ለማከም ጥሩ ሐኪም መሆን በራሱ በቂ አይደለም። በሽተኛውን አቅርቦ መመርመርና የበሽታውን ስር ማግኘት ይረዳልና ቀጣዮ ጉባዬ በፖለቲካ የተራራቀ አመለካከት ያላቸውን ወጣቶች መጋበዝና ሀሳባቸውን መረዳት ያስፈልጋል ለማለት ነው።

ይህንን ሀሳብ እዛው ውይይቱ ላይ በተነሳ አንድ ጥሩ ነጥብ ላጠናክረው።አንዲት እህት ለዶ/ር በያንና እና ለአቶ ሌንጮ የወረወረችው ጥያቄ በጣም ጠቃሚ ይመስለኛል።ባጭሩ የጥያቄዎ ሀሳብ የነበረው ወጣቶችን በርግጥ እናንተን ይሰሟችኾል ወይ የሚል አንድምታ ያለው ወሳኝ ጥያቄ ነው።ዛሬ በፖለቲካው አካባቢ ያለው ትውልድ በተለያዩ ቡድኖች ላለፉት ሶስት አስርት አመታት የጫካ ፖለቲካ ሲሰራበት የኖረ ትውልድ ነው። እንደሚታወቀው አንድ ዱር ቤቴ ያለ አማፂ ነፃ አወጣዋለው የሚለውን ማህበረሰብ ከጎኑ ለማሰለፍ ታሪኮችን ከማንሻፈፍ ጀምሮ በርካታ የፈጠራ ድርሳኖችን ወደ ሕዝብ ያሰራጫል። የህውሃትንና የሀውዜንን ታሪክ እንደ ምሳሌ መውሰድ እንችላለን። የተዛቡም ይሁኑ የተፈበረኩ የውሸት ታሪኮች ግነታቸውና ውሸትነታቸው ለመሪዎቹ (ለፈጣሪዎቹ) እንጂ ፖለቲካው ለሚሰራበት ወጣት እውነት እንሆኑ ነው የሚታመነው። ለዚህም ነው የፖለቲካ አቋምን ለመቀየር ለመሪ እንጂ ለተከታይ ከባድ የሚሆነው።ስለዚህ ዛሬ የአመለካከትና የእስትራቴጂ ለውጥ አድርገናል የሚሉን የፖለቲካ መሪዎች ወጣቱን ማስከተል እንደሚችሉ በምንም መልኩ እርግጠኛ መሆን አንችልም። እንደውም እውነታው እነዚህ የቀድሞ የፖለቲካ መሪዎች ዛሬ ባላቸው ለዘብተኛ የፖለቲካ አመለካከት ከስልጣን እንዲነሱና እንዲባረሩ የተደረጉ መሆናቸውን መዘንጋት የለብንም። በጫካ ፖለቲካ የለከፉት ትውልድ ግን የራሱን መሪ እየመረጠ ተመሳሳይ መዝሙር እየዘመረ ያለበት ሁኔታ ነውና ያለው ወጣቱን ቀጥታ ማቅረብና መመካከር ላይ ቢሰራ የሚሻል ይመስለኛል ለማለት ነው።

የመጨረሻውና ሶስተኛ ክፍተት የምለው ከሙሁራኑ በመቀጠል ድርጅታቸው የሚከተለውን የፖለቲካ ፍልስፍና እንዲያስረዱ የተመረጡት የፖለቲካ ፖርቲዎች የአመራረጥ ሂደት ላይ ይሆናል።በኮንፈረሱ ላይ የተስተናገዱት የፖለቲካ ፖርቲዎችን ዘግንና ሕብረ ብሔርን መሰረት አድርገው የተቋቋሙ ናቸው። ሕብረ ብሔር የሆኑት እንደ ግንቦት 7 አርበኞች ግንባር፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ እንዲሁም ከሀገር ውስጥ በ/ዶ መራራ ይወከላል ተብሎ ተጠብቆ የነበረው ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ (ምንም የዘውግ ፖርቲዎችን ያሰባሰበ ቢሆንም እንደ ሕብረ ብሔር ካየነው በማለት ነው) ናቸው። ሁለተኛው ደግሞ ዘውግ ላይ ከተመሰረቱት የፖለቲካ ፖርቲች የተወከሉት አሁንም በዶ/ር መራራ ይወከላል ተብሎ ተጠብቆ የነበረው የኦሮሞ ፌደራሊስት ፖርቲ እና የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ግምባር ናቸው።ሁለቱንም የፖለቲካ እርዮት አለም የሚያቀነቅኑ ፖርቲዎችን በአንድ መድረክ ላይ ሀሳባቸውን እንዲያቀርቡ መደረጉ በራሱ ችግር ባይኖርበትም የዘውግ ፖለቲካን ስናስተናግድ ግን ውክልናን ማመጣጠኑ ጠቃሚ ነገር ይመስለኛል። ወደድንም ጠላንም ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ዘርና ቋንቋን የተመለከቱ ጉዳዮች እንዲህ በዋዛ የሚታዩ ጉዳዮች አይደሉም።ስለዚህ ይህንን አይነት መድረክ ሲዘጋጅ አግላይ መሆን ያለበት አይመስለኝም።እርግጥ ነው ሁሉንም የዘውግ ፖርቲዎች ማስተናገዱ ከባድ ነው። ነገር ግን ለአለፉት 25 ዓመታት ምናልባትም ከሁሉም ሕዝቦች በተለየ መልኩ በገዢው መንስት በጠላትነት ተፈርጆ ቁም ስቅሉን እያየ ያለውን የአማራውን ማሕበረሰብ የሚወክል ድርጅት አለማካተቱ ስህተት ነው የሚሆነው። በመሰረቱ እኔ ሞረሽ የአማራ ድርጅት በጉባዬው ላይ መጋበዙንና አለመጋበዙን የማውቀው መረጃ የለኝም። ነገር ግን የሞረሽ ሰዎች ይህንን አይነቱን መድረክ ለመጠቀም ያቅማማሉ ብየ አላስብምና ምናልባት ግብዣው ካልደረሳቸው ወደፊት ታሳቢ እንዲደረግ ለመጠቆም ነው።

ብዙ ወገኖች የአማራን ማሕበረሰብ ለኢትዮጵያ አንድነት እንቅፋት ሊሆን አይችልም የሚል አመለካከት እንዳላቸው አውቃለሁ።አንድ መረሳት የሌለበት ነገር ቢኖር በአንድ ሀገር ውስጥ ከሚኖሩ ሕዝቦች መካከል  በአንደኛው ወገን የሀገርን አንድነት አደጋ ላይ የሚጥል የአቋም ለውጥ የሚከሰተው በዛ ሕዝብ ላይ ተለይቶ በሚፈፅም በደል መሆኑን ነው። ያለፉትን 25 ዓመታት የኢትዮጵያን ፖለቲካ ለተከታተለና በአማራ ሕዝብ ላይ የደረሰውን መከራ ለታዘበ እንደው ዝም ብሎ "አማራ አንድነቱን አይንድም" እያሉ ይህንን መሰል አግላይ ነገሮችን ማድረግ የዋህነት ነው። የፖለቲካውን ድባብ መርዳት ጥሩ ይመስለኛል።ልዩነቱ እንደ መፍትሄ እየቀረበና የብዙዎችን ድጋፍ እያገኘ ነውና ሰዶ ማባረር እንዳይሆን ጥንቃቄ ይደረግበት ለማለት ነው።

ቸር እንሰንብት

E-mail
gizdemelash@gmail.com

ኢትዮሚድያ - Ethiomedia.com
April 10, 2016